October 27, 2009

# ዓውደ ሃሳብ!

ከሐዋርያ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል፤

ክቡራትና ክቡራን ወገኖች፤ በያላችሁበት ሰላምታችን ይድረሳችሁ።

ብዙዎቻችሁ ሐዋርያን ታውቁልናላችሁ ብለን እናምናለን። ላለፉት 15 ዓመታት በሐዋርያ በኩል የተቻለውን ያህል ሁለገባዊና ውስብስብ ለሆነው የሀገራችን ሁኔታ መፍትሄ ለመሻት ተጥሯል። ጊዜያችን ለጉንጭ አልፉ ንትርክና አጉል ዝ ና ወመወደስ ሳናባክን አነሰም በዛ ቁም ነገር ላይ ለማዋል ጥረናል።

“ዓውደ ሃብ” ይባል የነበረ ዓምዳችን ለየት ባለ ዝግጅት እንደገና ለማስቀጠል አስበናል። ምክንያታችንም አበይት የሆኑና በተግባር ሊተረጎሙ የሚችሉ ጉዳዮቻችንን ለማወያየትና ለማበራየት ካለን ፍላጎት ተነስተን ነው። ጋዜጣው ሃይል ስላለው በዓምዱ ላይ የሰፈሩ ሃሳቦች ግምት ሊሰጣቸው ስለሚችል፥ ሰፋ ያለው የአንባቢ ክፍል እንዲሳተፍበት እያስገነዘብን፥ በተለይ ደግሞ ምሁራን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ እናሳስባለን።

የዝግጅቱ ሂደት እንዲህ ነው፡- መሪ የሆኑ ወቅታዊ ጥያቄዎችን ከአንባቢያን በየወሩ ሰብስበን መልስና አስተያየት እንዲሰጥባቸው በእምዳችን ላይ መልሰን ለእንባቢያን እናቀርባለን። የሚሰጡትን ገንቢ መልሶችና አስተያየቶችም በሚቀጥለው እትም ላይ ከሌሎች አዳዲስ ጥያቄዎችና ሃሳቦችና ጋር በአምዱ ላይ እንዲቀርቡ ይደረጋል፤ ሂደቱ በዚህ አይነት በአንድ ዓምድ ላይ በሚቀጥለው እትም መመለስ ያለባቸው አዳዲስ ጥያቄዎች እየቀረቡ፥ ላለፈው እትም ጥያቄዎች ደግሞ መልስና ማብራሪያ እየተሰጠ ይቀጥላል። ስለዚህም፥ አንባቢያን በአንድ በኩል ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ገንቢና በውል የተሰላ መልስ እንዲሰጡ ሲጠየቁ፥ በሌላ መንገድ ደግሞ በሚቀጥለው እትም መልስና ማብራሪያ ይዘው የሚቀርቡ ውይይት ጋባዥ ሃሳቦችንና ጥያቄዎችን እንዲያመነጩ እናሳስባለን።

ለመጀመሪያ የአምዱ እትም የሚሆኑ ጥያቄዎችን ዝግጅት ክፍሉ ከዚህ መሸኛ ጋር ከዚህ በታች ያቀርባል። አንባቢያን ማብራሪያ መልሳቸውንና ወደፊት የሚመለሱ አዳዲስ ጥያቄዎችን እንድትልኩልን በትህትና እናሳስባለን። አንድ አንባቢ የግድ ሁሉንም ጥያቄዎች መመለስና ጥያቄም ማቅረብ የለበትም፤ መልስ ሳይሰጥ ጥያቄ ማቅረብ ወይም ለሚመለከተው አንድም ይሁን ከዚያ በላይ ጥያቄ ብቻ መልስ መስጠት ይቻላል- ሁሉን ጥያቄዎች መመለስ የለበት/የለባትም።

## ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻ በዝግጅት ክፍሉ የቀረቡ ጥይቄዎች፤

1) የኢዮጵያ ፖለቲካዊ ችግር ምንድን ነው? እንዴትስ ሀገራችን ኢትዮጵያን መታደግ ተሳነ? ምን መደረግ አለበት?

2) አሁን ሀገራችን ውስጥ ያለው ሁለገብ ሁኔታ ምን ይመስላል? ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ብሄራዊ ምርጫ መካሄድ ይችላል?

3) ምሁር ማነው? ምሁርነት እንዴት ይገለጻል?

4) ከኢትዮጵያ ውጭ በተለያዩ ምክንያቶች ተሰዶ መኖር የጀመረው ህብረተሰብ ዝርያ ተበትኖ እንዳይቀርና ለሀገራችንም ተስፋ እንዲሆን ምን ማድረግ አለበት?

5) የኢትዮጵያ ሴቶች ይማረራሉ፥ "ደም" ያለቅሳሉ:: ችግራቸው ምንድን ነው? የማህበራዊ ሥርዓት ጥልመት? ወይስ የተፈጥሮ እርግማን? የሚጎርፍ እምባቸውን ለማስቆም ምን መደረግ ይኖርበታል?

## ማሳሰቢያ፤

- የቀን ገደብ:- በየወሩ 25ኛ ቀን ተጠናቆ መቅረብ ይኖርበታል::
- ቋንቋዋ:- በአማርኛ ይመረጣል - የእንግሊዝኛ ጽሁፎች ካልበዙ ተተርጉመው ይቀርባሉ፤
- የሚቀርቡ ጥያቄዎችና ሃሳቦች:- ሀገራዊና ሕዝባዊ ሆነው ማህበራዊ ኖሮን፥ ምጣኔ ሃብታዊና ፖለቲካዊ ሥንክሳሮችን መሠረት ያደረጉና የሚመረምሩ መሆን ይኖርባቸዋል::
- ጥያቄዎችና ሃሳቦች ከማጥቃት ወይም ከማሸማቀቅ የተገቱ ይሁኑ፤
- ጥያቄዎችና ሃሳቦች ነጻ የሆኑና ለሐዋርያ ብቻ የተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል::
- ይህ መልእክት ቢሳተፉ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብለው ለሚታሰቡ ወገኖች ሁሉ እንዲደርስ ተባበሩን፤
- መላኪያ:- hawarya.publications@sympatico.ca

ለሚደረግልን የጋራ ትብብር ከልብ እናመሰግናለን፤
የሐዋርያ ዝግጅት ክፍል